ብለው ያባረሯቸውን ክርስቲያን ወገኖቻቸውን ተራገሙ።" በማለት ነቢ
ሚሽድ የገለፀው።

ፓትሪያሪኩ እየሩሳሌምን ለቀው በሚሔዱበት ጊዜ በጣም ብዙ
ሃብትና ብዙ ሸንጣሎች ይዘው ነበር። ያን ሁሉ ሃብት ተሸክመው ነገር
ግን የተቸገሩና ቅጣቶቹን መክፈል ያልቻሉ ደሃ ወገኖቻቸውን
ለመርዳትና ለማስለቀቅ አንዲት ሳንቲም ለመክፈል ፍቃደኛ አልነበሩም።
ፒል ፓትሪያርኩን "ቅንጣት ህሊና የሌላቸው ሰውዬ" በማለት ነበር
የገለፃቸው። ፓትሪያርኩ ደሃ ወገናቸውን ለማስለቀቅ አንዲት ሳንቲም
ሳያወጡ፣ የተቸገረ አንድ ወገናቸውን ለመርዳት ቅንጣት ሳይሞክሩ፣
ሃብትና ንብረታቸውን አሸክመው ሲወጡ የተመለከቱ ሰዎች፦ "ለምን
ሃብታችሁን ነጥቀህ ለህዝባዊ ጉዳይ አታውለውም?" የሚል ጥያቄ
ለሰላሐዲን አትርፈውለት ነበር። ሰላሐዲን ግን "ታሊን ከማነኛ አሥር
ዲናር ማስከፈልን አመርማለሁ።" በማለት መለሰላቸው። እዚህ ላይ ፒል
"ሙስሊሙ ሱልጣን የክርስቲያን ቀሳውስቶችን የሞራልንና የመልካምነትን
ምንነት ያስተማረበት ገጠመኝ" በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል።

በመስቀለኞች የመጀመሪያ ወረራ ጊዜ ሙስሊሞች ያዩትን ስቃይና
መከራ በተመለከተ ቀደም ብለን መጥቀሳችን ይታወሳል። አልቲት ነበር
የተፈጸመባቸው። ሺዎች ተጨፈጨፉ። ደማቸው ጎርፍ ሁኖ ፈሰሰ።
አ.ሒ.አ በ492 (አ.ኤ.አ በ1099) እየሩሳሌምን ሲቆጣጠሩ የነበረውን
ሁኔታ የገለፀውን ሚሽድን በመጥቀስ እንግሊዛዊው የታሪክ ሀሐፊ
ያሰፈረውን ታሪካዊ ዕውነታ ልዑል ዓሊ እንዲህ በማለት ይደግመዋል፦

> ሙስሊሞች በየመንገዱ ተገደሉ። በየቤታቸው ተጨፈጨፉ።
> የተወሰኑ ሰዎች ከዕልቂቱ ለማምለጥ ከረጃጅም ግንቦች ላይ
> በደመነፍስ ይዘሉ ነበር። ሌሎቹ ነፍሳቸውን ለማዳን
> በመስጅዶችና በተለያዩ ቦታዎች ተደበቁ። ነገር ግን ክርስቲያኖች
> እያሳደዱ አንዳውሬ አደኗቸው። እግረኞች እና
>
> ፈረሰኞቻቸው በሙስሊሞች ሬሳ ላይ ተራመዱ። አምልጠው
> መደበቂያ ሥፍራ የሚፈልጉትን ሁሉ ለቀሚቸው። ሃብታቸውን
> ለመውሰድ ሲባል በሕያውት እንዲቆዩ ተደርገው የነበሩ
> ሙስሊሞች በሙሉ ተገደሉ። ሌሎች ደግሞ ከነሕይወታቸው

እሳት ተለኮሰባቸው። ከዚቶች ጣሪያ ላይ እየዘለሉ ለመፈጥፈጥ አስኪገደዱ ድረስ በእሳት ተቃጠሉ። የተቀሩት ሙስሊሞች ተደብቀው ከተቀመጡባቸው ቦታዎች እየተለቀሙ ወደ አደባባይ ወጥተው ከሌሎች ሬሳዎች ላይ ተደርበው ተገደሉ። ሴቶች አነዙ፤ ህፃናት አለቀሱ፤ ዒሳ (እየሱስ) (ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን) ለጠላቶቹ ይቅርታ ያደረገበት ቦታ በሬሳዎች ተሞላ።"

ሚል እንዲህ በማለት ይጨምራል

"ምንም ጥሩት ሳያፈሰሙ ተጨፍጭፈው ላለቱት ለእነዚያ ሰዎች ያዘነም ሆነ የተጨነቀ አንድም ሰው አልነበረም። ሰባት ሺህ ንፁሃን ሰዎች ያለርህራሄ ተገደሉ።"

ለእንደዚህ ዓይነት ጨካኝ ጠላቶች ስላሉዲን ያደረገውን ዓይነት ይቅር ባይነት እና ሰጋስነት አይተው ያውቃሉን?

እየሩሳሌም፤ የኛም የናንተም ነበረች

በኛ ፍትህ ሰፈነባት፤ በናንተ ግን በደም ታጠበች

እናንተ፤ ፈቃዳችሁ እንዲገደሉ ምርኮኞች

እኛ፤ ይቅር አልናችሁ አከሰን መልካም ሥራዎች

የናንተና የኛ ልዩነት፤ ይኸው ብቻ በቂያችን

ዕቃ ቢከነበል የያዘውን፤ ሰውም ቢሰጥ ያለውን

ሐቲ እንዲህ በማለት ምልከታውን ይቋጫል። ከሰማንያ ስምንት ዓመት በፊት የመስቀል ወራሪዎች ሙስሊም ነዋሪዎችን የያዙበት ሁኔታ፤ ሙስሊሞች ወራሪ ክርስቲያኖችን ከያዙበት ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ልዩነታቸው እጅግ በጣም ግልፅ ነበር።

የአዘራ መከበብና ሦስተኛው የመስቀል ዘመቻ

የመስቀል ወራሪዎች እየሩሳሌምን፤ አከሬን እና ሌሎች ከተማዎችን ጥለው በሙስሊም ወታደሮች ጥበቃ እየተደረገላቸው ሴባኖስ ውስጥ ወደ ምትገኘው ታሃር ድረስ መሸንታቸውን ቀደም ብለን ጠቅሰን ነበር።

ምንም እንኳ የሰላም ስምምነት የፈረሙና የተቀበሉ ቢሆንም መስቀሎቹ ታላቸውን አጠፉ፤ ስምምነታቸውን አፈረሱ።

ታሪር ላይ ተሰባስበው፤ ከሰላሐዲን ጋር የነበራቸውን ስምምነት አፍርሰው፤ በሸፍጥ ተሰማሙ። ወደ አክሬ አትንተው ዙሪያዋን ከበቧት። ከአውሮፓ የተደረገላቸውን የስንቅና የትጥቅ እገዛ በመጠቀም ወታደሮቻቸውን እንደገና አደራጅተው ከአውሮፓ ከተላከው ሠራ ጋር በማበር ከበቧት። ከበባው ሁለት ዓመት መቆየቱና ሁለቱም ወገኖች ያልጠረ ጥንካሬያቸውን ያሳዩበት በመሆኑ በታሪክ ውስጥ ገልህ ቦታ ለመያዝ በቅቷል።

አ.ሒ.አ በ585 በረጅብ ወር ሰባተኛ ቀን ላይ (አ.አ.አ በ1189) ወደ አክሬ በማምራት በየብስና በባህር ከበቧት። የሙስሊሙ ሠራዊት ግን ዝግይቶ ደረሰ። ሰላሐዲን ጠል-ኪሳን ተብላ በምትጠራው ኮረብታ ቦታ ላይ የእዙ ማዕከል የሆነችውን ድንኳን አሰረ። ሠራዊቱ በየብስ በኩል ብቻ እንዲያጥራቸው አደረገ። መተነኳኮሱና መጋፈጡ ተጠለ። በሁለቱም ወገን ግብግቡ ተጋጋለ። ነገር ግን አንዳቸውም ጦርነቱን በአሸናፊነት ሳይቋጨ ብዙ ጊዜ አለፈ። ሰላሐዲን የተወሰኑ ወታደሮቹን የግዛቱ አካል ወደ ሆኑትና ጠርዝ ላይ ወደሚገኙት አካባቢዎች እንዲሔዱና ህዝቡ በጀሃድ እንዲሳተፍ እንዲያሳስቡ ላካቸው። እየሩሳሌም ከመስቀል ወራሪዎች እጅ ነፃ መውጣቷን ሲሰሙ ተስፋ ቆርጠውና እረፈው ተቀምጠው የነበሩት አውሮፓዊያኑ በበኩላቸው አክሬንን ለከበበው መስቀሎች ጦር የስንቅና የትጥቅ አቅርቦት አደረጉ።

ሁለቱ ወገኖች በአክሬ ዙሪያ በሚታገሉበት ጊዜ ግን የአውሮፓ ንጉሶች ለሦስተኛው የመስቀል ዘመቻ እየተዘጋጁ ነበር። ይህን ዘመቻ ከቀደሙት ሁለት ዘመቻዎች ልዩ የሚያደርገው፤ ዘመቻውን የመሩት በዘመኑ አውሮፓ ውስጥ የነበሩት ሦስቱ ትላልቅ ንጉሶች መሆናቸው ነው። የጀርመኑ ንጉሰ ነገስት ፍሪድሪክ፤ ባርባሮሣ፤ የፈረንሳዩ ንጉሰ ፊሊፕ አውግስተስ እና የእንግሊዙ ንጉሰ ልበ ሙሉው ሪቻርድ።

የጀርመን ዘመቻ

የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት እና አንድ መቶ ሺህ ወታደሮችን የያዘው ሠራዊቱ በሐንጋሪ በኩል አልፈው ወደ ኮንስታንቲኖፕል አመሩ። ይህ ሠራዊት የቤዛንታይኑን ንጉሠ ነገሥት ኢሳቅ ሁለተኛ ሥጋት ፈጥሮበት ነበርና ሠራዊቱን ለመተባበርም ሆነ መንገድ ለመምራት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። በዚህ ብቻ አላበቃም። ጀርመኖች ወደሱ እየመጡ መሆናቸውን ለሰላሑዲን ነገረው። ምንም ዓይነት ትብብር እንዳላደረገላቸውም ገለፀለት። የጀርመኑ ጦር ትንሿን ኤዥያ (Asia minor) አቋርጦ፣ በአርመኒያ ተራራዎች ውስጥ ሲማስን ንጉሠ ነገሥቱ በሳሊፍ ወንዝ ተወስዶ ሞተ። ከንጉሠ ነገሥቱ ሞት በኋላ ሠራዊቱ ተበታተነ። የተወሰኑት ወደ ጀርመን ተመለሱ። ሌሎች ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ተከትለውና በመርከቦች ተጭነው ወደ አክሬና ታይር አቀኑ። የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ፍሬድሪክም ሞተና ጥቂት ወታደሮች ብቻ ገቢቸውን አጠናቀው አክሬ መድረስ ቻሉ። ሙሉ ለሙሉ መድረስ ችለው ቢሆን ኑሮ ምናልባትም ሁኔታዎች በጣም ከባድ ይሆኑ ነበር።

የፈረንሳይ እና የእንግሊዝ ሠራዊቶች

የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሠራዊቶች ሲሲሊ ላይ ተገናኙ። አክሬንን የከበቧት መስቀለኞች እየጠበቋቸው ቢሆንም በሁለቱ መካከል የተፈጠሩ ልዩነቶችን መፍታት አቅቷቸው እዚያው ሲሲሊ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተቀመጡ። በመጨረሻ የፈረንሳይ ወታደሮች ሲሲሊን ለቀው ሔዱ። ከአሥር ቀናት በኋላ እንግሊዞችም ተከተሏቸው። የፈረንሳይ ጦር አክሬ ሲደርስ መስቀለኞች በደስታ ጨፈሩ።

የእንግሊዝ ንጉሥ ሪቻርድ በከባድ ዝናብ እና ውሽንፍር ምክንያት በጊዜው በቤዛንታይን ቁጥጥር ሥር ወደነበረችው ወደ ሳይፕረስ ለመጠጋት ተገደደ። ልበ-ሙሉው ሪቻርድ የቤዛንታይኖች ተቃውሞ ቢገጥመውም ማሽነፍና ሳይፕረስን መያዝ ችሎ ነበር። ለትንሽ ጊዜ ተረጋግቶ ከተቀመጠባት በኋላ በሰላሑዲን ተማርኮ የተለቀቀውና ስምምነቱን አፍርሶ አክሬን የከበባት ንጉሥ ላቀረበለት የእርዳታ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ወደ አክሬ ገሰገሰ።

የሙስሊሞች ተጋድሎ

የእንግሊዝ ወታደሮች ሲደርሱ ያለጥርጥር የወራሪዎች ኃይል ተጠናከረ። ሰላሑዲን አክሬን በወራሪዎች ላለማስያዝ ሲታገሉ እና ሲከላከሉ ለቆዩት ነዋሪዎቿ ለመድረስና ከበባውን ለመስበር ያደረጋቸው ጥረቶች በሙሉ ሳይሳኩለት ቀሩ። የእንግሊዞች መድረስ ደግሞ አክሬን የማዳን ጥረቱን የበለጠ አከበደበት። የአክሬ ነዋሪዎች ተስፋ ቆርጠው እጅ ለመስጠት ተገደዱ።

በዕለተ ጁሙዓ በወርሃ ጁማዱ-ሳኒ 17 እ.ሒ.አ በ587 (እ.ኤ.አ በ1191) ሰላሑዲን ስለ አክሬ ነዋሪዎች ሁኔታ ከአማካሪዎቹ ጋር እየመከረ በነበረበት ሰዓት አክሬ በወራሪዎች እጅ ወደቀች። በግንቦቿ ላይ ባንዲራዎቻቸውን አውለበለቡ። ሙስሊሞች ተጨነቁ። ወራሪዎች ፈነጠዙ። አሁንም አረመኔያዊ ድርጊቶች ተደገሙ። አክሬ ነዋሪዎቿ በመስቀል ወራሪዎች ሲታረዱ በዝምታ ተመለከተች። መስቀለኞች ሰላሑዲን የዋለላቸውን ውለታ ረስተው፣ መልካም ሥራውን ዘንግተው፣ የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው፣ ግዴታዎቻቸውን ወዲያ ጥለው፣ በሙስሊሞች ላይ የጭካኔ በትራቸውን አነሱ። የእንግሊዙ ልበ ሙሉው ንጉስ ሪቻርድ ብቻውን እ.ሒ.አ በወርሃ ረጀብ 23 ቀን 587 (እ.ኤ.አ 16 ኦገስት 1191) ብቻ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሙስሊሞችን ገደለ። ውድ አንባቢ ሆይ! አክሬ ውስጥ በመስቀል ወራሪዎች ስለተፈፀመው ጭካኔያዊ ተግባር በትክክል የሆነውን ማወቅ ከፈለጉ ፑል ራሱ የፃፋቸውን ገፆች ይግለጡ! ፑል እንዳለው፡- ወራሪዎች አክሬ ውስጥ ስድስት ሺህ ሙስሊሞችን ገድለዋል። በጣም ብዙ ሐብት ያላቸውን ጥቂት ሰዎች ብቻ እንጂ አንድም ሰው አላተረፉም ነበር። እንደተለመደው የመስቀል ወራሪዎች አክሬን ሲይዙ በደስታ ጨፈሩ። ሚሹድ እንዲህ በማለት የፈንጠዝያቸውን ልክ ይነግረናል፡- ድል የቀናቸው የመስቀል ወራሪዎች ሌቫንትን ከረገጡ ጀምሮ በደስታ የሚይዙት የሚጨብጡት አጡ። አለቅጥ ፈነጠዙ። የተትረፈረፉት የምግብ ዓይነቶች፣ መጠጦችና በቅርበት ከሚገኙ ደሴቶች ያመጧቸው እንስቶች ወደ አክሬ የመጡበትን ዓላማና ወደፊት የሚጠብቃቸውን ሥራ ፍፁም አስረሷቸው።

ስራዊታቸው ከአከራ ድል በኋላ የተቀዳጀው የአሸናፊነት ስሜት፣ የአውሮፓዊያን የተጠናከረ ድጋፍ፣ ኢሽያ ውስጥ የሚገኙ የላቲን ግዛት ከዚህ ሠራዊት ጎን መቆማቸውና ሌሎች ብዙ ጠላቶች በሳላሑዲን ላይ መነሳታቸው ሲታይ በአጭር ጊዜ ውስጥ መስሊሞችን ደምስሰው ድሮ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ያመለሳሉ የሚለው ግምት አይሉ ነበር። ነገር ግን በሁለት የጦርነት ዓመታት ውስጥ ከአንድ ከተማ ውጭ ማስለቀቅ አልቻሉም ነበር። ምንም እንኳን በሰላሑዲን ጥቂት ምርጥ ወታደሮቹን ቢያጣም በዕናት ተዋያቱ። ሠራዊቱ በጀግንነት ተጋደለ።

የመስቀል ወራሪዎች ሌሎች ተጨማሪ ከተማዎችን ለመያዝ ያደረጓቸው ሙከራዎች በሙሉ ካልተሳከቡትና ድላቸውን ካዘሞባቸው ምክንያቶች ውስጥ በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ ንጉሶች መካከል ሲሲሊ ውስጥ ጅምሮ የተጠሰው አለመስማማት እንደ አንድ ምክንያት ያጠቀሳል። ሌላውና ከባዱ ምክንያት ደግሞ በእየሩሳሌሙ ንጉስና በታየሩ ገዥ ማርኳስ ኮንራድ ሞንቱ የተፈጠረው አለመግባባት ነበር። የእንግሊዙ ንጉስ ለእየሩሳሌሙ ንጉስ የበለጠ ያደላ ነበር። የፈረንሳዩ ንጉስ ደግሞ ለታየሩ ገዥ ያደላ ነበር። የታየሩ ገዥ እየሩሳሌም ላይ የመንገስ ፍላጎት ነበረው። አከራን ከያዙ በኋላ ግን ኮንራድ ሞንቱ ሊተካው ተስማሙ። በዚህ ሁሉ መሀል የፈረንሳዩ ንጉስ ሪቻርድ የቀረው ወንጅል ያለ ይመስል በዘመቻው ቀጠለ። በሰላሑዲን እጅ የሚገኙ ከተማዎችን ለማስለቀቅ ፈልጓል። በሁለቱ መካከል በርካታ ጦርነቶች ተደረጉ። እንደ አርሱፍ ጦርነት የከበደ ጦርነት ግን አልነበረም። አርሱፍ ውስጥ መስቀለኞች ድል ቀናቸው። መስቀለኞቹ ይህን ድል የሐሪነጢን ሽንፈታቸው ማካካሻ አድርገው ወስደውት ነበር።

የጦርነቱ ማብቃት

በሁለቱ ወገኖች ግጭቶች ቀጠሉ። የመስቀል ወራሪዎች ብዙ ጊዜ ከእየሩሳሌም ጎግ ድረስ እየመጡ ተመለሱ። የእንግሊዙ ንጉስ የሆነ ሴራ ተሴርቦባቸዋል፣ ወጥመድ ተዘጋጅቶልናል፣ እየሩሳሌምን እየተከላከሉ ያሉት ከአሁን በፊት ያልነበሩና የተለዩ ናቸው ብሎ ስላሰበ እየሩሳሌምን መክበብና ሰብሮ መግባት ላያስችል ቀረ። የግጭቶች ውጤት ሁለቱን ወገኖች ወደ አንድ ነጥብ አመጣቸው። የመስቀል ወራሪዎች

እየሩሳሌምንም ሆነ ሌሎች ከተማዎችን መያዝ አልቻሉም፣ ሰላሑዲንም ቢሆን እነሱን አሸንፎ ወደ ባህር ዳርቻዎች መግፋት ወይም ባህር ውስጥ መጨመር አልቻለም ነበር። በዚህ ምክንያት ሁለቱ ወገኖች መደራደር ፈለጉ፣ ነገር ግን በስምምነቱ የተወሰኑ ነጥቦች ላይ መስማማት አቃታቸው። በመጨረሻ አ.ሒ.አ 588 (አ.ኤ.አ 1192) ራመላህ ውስጥ ስምምነት ተፈራረሙ። ከተስማሙባቸው ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት ወሳኝ ነጥቦች ይገኙበት ነበር፡-

- የመስቀል ወራሪዎች ከታየር እስከ ሐይፋ ያሉትን የባህር ዳርቻዎች ይወስዳሉ።
- ክርስቲያኖች ምንም ዓይነት ግብርም ሆነ ክፍያ ሳይጠየቁ እየሩሳሌምን መጎብኘት ይችላሉ።
- የስምምነቱ ጊዜ ሦስት ዓመት ከስምንት ወር ድረስ የፀና ይሆናል።

በፍራንኮች ተይዘው የነበሩ የባህር ዳርቻዎች የቀድሞዋ እየሩሳሌም የግዛቷ አካል ተደርገው ተወሰዱ። አክሬ የአዲሲቷ እየሩሳሌም የግዛቶቿ ዋና ከተማ ሆነች። በሦስተኛው ዘመቻ ዝናው ናኝቶ የነበረው ልቡሙሉው ሪቻርድ ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ወደ እንግሊዝ ተመለሰ።

በርካታ ሰዎች ያለቁበት፣ ከተማዎች የፈረሰብት፣ የጀርመኑ ንጉሰ ነገስት ወንዝ ውስጥ የሰጠመበት እና ፈረንሳይና እንግሊዝ ምርጥ ወታደሮቻቸውን ያጡበት ይህ ሦስተኛው የመስቀል ዘመቻ ከአምስት ዓመታት በኋላ በዚህ ሁኔታ ተጠናቀቀ።

በእነዚያ አምስት ዓመታታ ውስጥ ፍራንኮች አክሬን ከመያዝ ውጭ ሌላ ምንም አላገኙም ነበር። አውሮፓ ትልቅ ኪሳራ ደርሶባት ነበር። ምክንያቱም በአጠቃላይ ሲታይ ካገኙት ያጡት ይበዛ ነበር። ሙስሊሞች በበኩላቸው ሰላሑዲን ከመምጣቱ በፊት በፍልስጤም ምድር ውስጥ መቆሚያ ስንዝር ቦታ አጥተው ነበር። አሁን ከሒጥጢኑ ወሳኝ ጦርነት በኋላ እና ራመላህ ውስጥ ከተደረገው ስምምነት በኋላ ድፍን ፍልስጤም ተመልሳ በእጃቸው ገባች። በታየርና በአክሬ መካከል ከምትገኘው ጠባብ ክፍል ውጪ ተነጥቀው የነበሩትን በሙሉ እንደገና አገኙ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰላሑዲን ቂሳራዊያንን እንበርክኳልና፣ የመስቀል ወራሪዎችን ቀጥቶ አባሯልና፣ እየሩሳሌምን ሰባለቤቱ መልሷልና፣ የኢስላምንና የሙስሊሞችን ክብርና ኃያልነት አድሷልና እንዲሁም ስሜን ኢራቅን (ኩርድን)፣ የሌቫንትን አብዛኛውን ክፍል፣ ታላቋን ሶሪያ፣ ግብፅን፣ ፍልስጤምን፣ የመንን እና ባርቃህን ያካተተ ሠፊ ግዛት መመስረት ችሎ ነበርና ከታላቅ ስብዕናዎች ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ያለው ስብዕና ሆነ። በጣም የሚገርመው ደግሞ በጣም ባጭር ጊዜ ይህን ሁሉ ማሳካቱ ነበር።